በየካ ክክፍለ ከተማ ወረዳ **08** ብሩህ ተስፋ ጉድኝት ማዕከል የወጣቶች ገነት ቅ/ኢ/ኢ/ደ/ት/ቤት የ **2016** ዓ፣ም የአንደኛ ሴሚስተር የ **6** ኛ ክፍል ግብረ ገብ የሞዴል ፈተና

ስም ---------- ክፍል ---------- ቁጥር -------

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች

ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጪ

---------1/ ከሚከተሉት አማራጮች አንዱ የግብር ስወራ የሚደረግባቸው መንገዶች ውስጥ አይካተትም

ሀ/ ሰነድ ማጭበርበር ለ/ ገቢን መቀነስ

ሐ/ የተጋነነ ወጪ መ/ ደረሰኝ መጠቀም

---------2/ ከሚከተሉት ውስጥ የግብር ስወራ የሚያስከትለው ጉዳት የቱ ነው?

ሀ/ ሙስና ያስፋፋል ለ/ የሃገርን እድገት ይጎዳል

ሐ/ ወንጀለኛ ያደርጋል መ/ ሁሉም መልስ ነው

----------3/ አንድ ማህበረሰብ ባህሉንና እምነቱን ማሳደግ የሚችለው

ሀ/ የሃይማኖት አባቶች ሲኖሩት ሐ/ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ሲኖር

ለ/ የህግ ተገዢነት ሲኖር መ/ ሁሉም መልስ ነው

----------4/ አገልግሎት ሳይሰጡ በተሳሳተ መንገድ ገንዘብ መውሰድ ምን ይባላል?

ሀ/ ጉቦ ለ/ ማጭበርበር ሐ/ ሙስና መ/ ግብር ስወራ

----------5/ ያልተገባ ገንዘብ ለማግኘት በተሳሳተ መንገድ ገንዘብ መሰብሰብ ምን ይባላል?

ሀ/ ሙስና ለ/ ጉቦ ሐ/ ማጭበርበር መ/ ፍትህ

----------6/ ስልጣንን ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ተጠቅሞ ጓደኛን ወይም ቤተሰብን መጥቀም ምን ይባላል?

ሀ/ ሙስና ለ/ ወገንተኝነት ሐ/ ጉቦ መ/ ማጭበርበር

----------7/ ግለሰቦች የሚፈፅሙት ያለመታመን የወንጀለኝነት ባህሪ የሆነው የቱ ነወ?

ሀ/ ጉቦ ለ/ ሙስና ሐ/ ማጭበርበር መ/ ወገንተኝነት

----------8/ ---------- ተግባር ላይ ካላዋሉ የህዝቦች ነፃነትና ንብረት ለመጠበቅ አይቻልም።

ሀ/ ነፃነትን ለ / ህጎችን ሐ/ ፍትህን መ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው

----------9/ ከሚከተሉት አንዱ መልካም ሰዎች እንዲፈጠሩ ይረዳል

ሀ/ የህግ ተገዢነት ለ/ ሰላም ሐ/ ነፃነት መ/ ፍቅር

---------10/ በአፍ የሚወሰድ የሰው ልጅን አእምሮና አካል ሊጎዳ የሚችል ነገር ነው

ሀ/ ጦርነት ለ/ ሙስና ሐ/ አደንዛዥ ዕፅ መ/ ሰላም

----------11/ የህፃናት ህገ ወጥ ዝውውርን መከላከልና መቆጣጠር የሚችለው ማነው?

ሀ/ ወላጅ ለ/ ህብረተሰብ ሐ/ መንግስት መ/ ሁሉም

----------12/ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንዱ አደንዛዥ ዕፅ ውስጥ አይደለም

ሀ/ አረቄ ለ/ ጫት ሐ/ ሲጋራ መ/ ቡና

----------13/ የህዝቦች ህይወት ፤ ነፃነትና ንብረት ሊጠበቅ የሚችለው ምን ሲኖር ነው?

ሀ/ ህግ ለ/ ምሉዕነት ሐ/ ሃብት መ/ ችሎታ

----------14/ በህገወጥ የህፃናት ዝውውር የተወሰዱ ህፃናት በምን ተግባር ላይ ይሰማራሉ?

ሀ/ በጉልበት ብዝበዛ ለ/ በወሲብ ስራ ላይ ሐ/ በልመና መ/ ሁሉም

----------15/ አደንዛዥ እፅ መጠቀም የሚያስከትለው ጉዳት የቱ ነው?

ሀ/ የአዕምሮ ህመም ለ/ ማህበራዊ ቀውስ

ሐ/ የኢኮኖሚ ቀውስ መ/ ሁሉም

----------6/ ---------- ከጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ ራስን ማስተዳደር ነው።

ሀ/ ሰላም ለ/ ፍትህ ሐ/ ሉአላዊነት መ/ የዜጎች ፍላጎት

----------17/ ከሚከተሉት አንዱ የመንግስትን ስልጣን ይገድባል

ሀ/ ሉአላዊነት ለ/ ህግ ሐ/ ሙስና መ/ ግብር

----------18/ ከሚከተሉት አንዱ የህግ ተገዢነት ዋንኛው ውጤት ነው

ሀ/ ፍቅር ለ/ ህግ ሐ/ ሰላም መ/ ፍትህ

----------19/ መንግስት ለዜጎች የሚያቀርበው አገልግሎት በምን ይወሰናል?
ሀ/ በግብር አሰባሰብ ለ/ በሰዎች ሃብት
ሐ/ ራስ ባለው ሃብት መ/ የማዕድን ሃብት
---------20/ ግብረ ገባዊ እኩልነት ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን ከሌሎች ሰዎች --------- እንደሆኑ ያምናሉ።
ሀ/ በላይ ለ/ እኩል ሐ/ በታች መ/ ሁሉም
----------21/ በሌሎች ልፋት የሚገኝ ትርፍን የመሰብሰብ አላማ የሌለው የቱ ነው ?
ሀ/ ግብረ ገባዊ ምሉዕነት ለ/ ሙሰኞች
ሐ/ በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች መ/ ሁሉም
---------22/ የሰዎች እምነቶችና አስተሳሰቦች ውጤቶች ናቸው
ሀ/ መልካም ባህሪያት ለ/ የነፃነት እጦት ሐ/ ህገወጥ ድርጊት መ/ ግብር ስወራ
---------23/ መልካም ባህሪ ያለው ሰው መገለጫ የቱ ነው
ሀ/ ምዕሉነት ለ/ ታማኝነት ሐ/ ሀቀኝነት መ/ ሁሉም
--------24/ አላስፈላጊ ውስጣዊ ግፊትን ፣ስሜትንና ምኞትን የመያዝ ብቃት ነው
ሀ/ ተጠያቂነት ለ/ ራስን መቆጣጠር ሐ/ ምሉዕነት መ/ ታማኝነት
--------25/ በእውነተኝነት ላይ የተመሰረተ ንግግር መናገር መተግበር ነው
ሀ/ ታማኝነት ለ/ ሀቀኝነት ሐ/ ማክበር መ/ ፍትሀዊነት
---------26/ አክብሮት መጀመር ያለበት ከማን ነው
ሀ/ ከቤተሰብ ለ/ ከጓደኛ ሐ/ ከራስ መ/ ከእናትና አባት
--------27/ የግብረ ገብ መርሀዎችን ለመተግበር የሚያስችል ብቃት የማን ነው
ሀ/ የመልካም ሰው ለ/ የመንግስት ሀላፊዎች
ሐ/ ለህግ ተገዢ መሆን መ/ የመምህራን
--------28/ ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጵያ የሚገኝ የግብረገብ እሴፍት ነው
ሀ/ እውነት መናገር ለ/ እንግዳ ተቀባይነት
ሐ/ ስርአት ያለው አለባበስ መ/ ሁሉም
--------29/ ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ህግ ተገዢነት ትክክል ያልሆነው ሀሳብ የቱ ነው
ሀ/ ህግ ሰዎችን ከጉዳት ይከላከላል ለ/ ህግ የሰዎችን ፍላጎት ይገድባል
ሐ/ ህግ ንብረታችንን ይጠብቃል መ/ ሁሉም መልስ አይደለም
--------30/ የት/ቤቱን ህግና ደንብ ማክበር ግዴታ የሌለበት ማን ነው
ሀ/ ተማሪ ለ/ መምህር ሐ/ አስተዳደር ሰራተኛ መ/ መልስ የለም
---------31/ ከሚከተሉት ውስጥ የተማሪዎች መብት ያልሆነ የቱ ነው
ሀ/ የት/ቤቱን ንብረት መጠቀም ሐ/ ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም
ለ/ የግል ንጽህናን መጠበቅና ማጽዳት መ/ ሁሉም መልስ ነው
--------32/ የህግ ተገዢነት አለመኖር ከሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ውስጥ አይካተትም
ሀ/ የፍትህ እጦት ለ/ ህገወጥ የህፃናት ዝውውር
ሐ/ አደንዛዥ እጽ መ/ የሰብአዊ መብት ክብር
-------33/ ሌሎች እንዲያደርጉልህ በምትፈልገው መንገድ ሌሎችንም እንዲሁ ማድረግ ምንን ይገልፃል ?
ሀ/ ምሉዕነት ለ/ ማክበር ሐ/ እሴት መ/ ተጠያቂነት
--------34/ የመልካም ሰው መለያ ባህሪያት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው
ሀ/ የሌሎችን ንብረት መጠበቅ ለ/ ሀቀኝነት
ሐ/ ለሌሎች ክብር መስጠት መ/ ሁሉም
--------35/ ጠንካራ የግብረገብ መርሀዎች ያሉትና እውነትን የሚከተል ሰው መገለጫ የቱ ነው
ሀ/ ሀቀኝነት ለ/ ምሉዕነት ሐ/ ታማኝነት መ/ ራስን መቆጣጠር

--------36/ ለሌላ ሰው ክብር የመስጠት መገለጫ የቱ ነው
ሀ/ ታማኝነት ለ/ ምሉዕነት ሐ/ ህግ አክባሪነት መ/ ራስን መቆጣጠር
---------37/ በእውነት ላይ የተመሰረተ ንግግርን መናገርና ተግባርን የመፈፀም ብቃትን የሚገልፀው

የቱ ነው

ሀ/ ታማኝነት ለ/ ሀቀኝነት ሐ/ ምሉዕነት መ/ ክብር

--------38/ ሰዎችን በተለየ መስፈርት ምክንያቶች በመጠቀም ለማበላለጥ ሳይሞክሩ በእኩል ማክበር ማለት

ሀ/ የግብረገብ ምሉዕነት ለ/ በራስ መተማመን

ሐ/ ታማኝ መሆን መ/ እውነተኛ መሆን

--------39/ እውነተኛ ግብረገባዊ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ባህሪያት ውስጥ አይካተትም

ሀ/ በሰዎች መካከል ልዩነት ይፈጥራሉ ለ/ ቃላቸውን ወደ ተግባር ይቀይራሉ

ሐ/ ለራስ መተማመናቸው የዳበረ ነው መ/ ሁሉም መልስ ናቸው

--------40/ ከህግ ከለላ የሚሰጠው የህይወት መሰረታዊ ጉዳይ የቱ ነው

ሀ/ ሰላም ለ/ ነፃነት ሐ/ ሉአላዊነት መ/ እውነተኛ መሆን

አዘጋጅ ወጣቶች ገነት ት/ቤት